# <u>አምባገነን መሪዎች በመጨረሻዋ የጣዕረ ሞት ሰዓት</u>

ከንጉሤ ጋማ

የኢትዮጵያዉ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ከዉጭ አገር ጋዜጠኞች ለቀረቡላቸዉ ጥያቄዎችና በተወካዮች ምክር ቤት ተብዬዉ ዉስጥ ከሰጧቸዉ መልሶች መካከል ጥቂቶቹን በአንክሮ ያጤነ ሰዉ የሚረዳዉ አንድ እዉነት አለ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገደብ የሌለዉ አምባገነናዊ ትምክህት ያደረባቸዉ መሆኑን፡፡

መለስ ዜናዊ ወደ ስልጣን ከመጡበት ወቅት ጀምሮ ለዜጎች ያላቸዉን ትዕቢትና ከአንድ መሪ የማይጠበቅ መረን የለቀቀ አነጋገራቸዉን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያዉቃል፡፡ የሰሞኑ ግን ገደቡን ያለፈ ነዉ፡፡ ተስፋ የቆረጡ አምባገነኖች የመጨረሻ ሰዓት ከዚህ እንደማይዘል ግልፅ ነዉ፡፡ ካልተገራ መረን አንደበታቸዉ የወጡት መልሶች **የዉድቀት ቀዳሚዉ ምልክት ማንአለብኝነት የነገሰበት ትምክህት** እንደሆነ ያነበብኩትን አንድ ጽሑፍ አስታወሰኝ፡፡ **Pride Will Come Before the Fall** http://www.bible-knowledge.com/pride-before-fall.html

ማንአለብኝነት የነገሰበት ትምክህት ወይንም ኩራት ያደረባቸዉ ግለሰቦች እራሳቸዉን ከማንም በላይ አዋቂ፣ ትልቅና ፈላጭ ቆራጭ አድርገዉ የሚቆጥሩ እራስ ወዳዶች ሲሆኑ በተቃራኒዉ ሌሎችን በበታችነት ዝቅ አድርገዉ የሚመለከቱ ናቸዉ፡፡ በሰዎች እኩልነት አያምኑም፡፡ ይህ ደካማ ባህሪይ መድሃኒት ከማይገኝለት፣ በየደረጃዉ በሰዉነት ዉስጥ እየተስፋፋና ስር እየሰደደ በመሄድ ለሞት ከሚያበቃ የካንሰር በሽታ ጋር ይመሳሰላል፡፡ በማን አለብኝነት መንፈስ የሚያድርባቸዉ ከንቱ ትምክህት ስሜታቸዉን፣ ተግባራቸዉንና ምግባራቸዉን በመቆጣጠር የአዕምሯቸዉን የመወሰን ደረጃ ይጋርደዋል፣ ያጨልመዋል፡፡ በዚህም ደረጃ ላይ እዉነትን ከስህተት መለየት ይሳናቸዋል፡፡ እዉነት ብለዉ የሚቀበሉት የተጋረደ ወይንም የጨለመ አስተሳሰባቸዉ የሚነግራቸዉን ብቻ ይሆናል፡፡ እራሳቸዉን ለሁሉም ነገር መልስ መስጠት የሚችሉ ትንሹ እግዚአብሄር አድርገዉ ይቆጥራሉ፡፡ ሃሳባቸዉን ከግብ ለማድረስ እንቅፋት ይሆንብኛል የሚሉትን ሁሉ በጠላትነት ይመለከታሉ፣ ህግ ይሽራሉ፣ ይጥሳሉ፡፡ ይጠቅመኛል፣ ይረዳኛል የሚሉትን ህግ ያወጣሉ፡፡ ከህግ በላይ በመሆን ዙሪያቸዉን ለከበበዉ ሁሉ ግምት ያጣሉ፡፡ ማንም ሊያቆማቸዉና ሊቆጣጠራቸዉ እንደማይችል ያምናሉ፣ እግዚአብሄርን ጭምር፡፡ የቅርብ ጓደኞቻቸዉንና ወዳጆቻቸዉን ይረሳሉ፣ ከአጠገባቸዉ ያስወግዳሉ፡፡ ከየት እንደመጡ መነሻቸዉን ይዘነጋሉ፣ ወደ አለሙት ወይንም ወደሚጓዙበት ለመድረስ የማንም እርዳታና ትብብር የእግዚአብሄርም ጭምር እንደማያስፈልጋቸዉ ይሰማቸዋል፡፡ በጠቅላላዉ ባላቸዉ ጥበብና ኃይል ዓለምን ለማሸነፍ ብቃት ያላቸዉ አድርገዉ እራሳቸዉን ይቆጥራሉ፡፡

ይህ በማን አለብኝነት ስሜት ዉስጥ ለወደቀ ትምክህተኛ የተሰጠዉን ትንታኔ ከኢትዮጵያዉ አምባገነን መሪ የቅርብ ጊዜ ባህሪይ ጋር ያለዉን ተመሳሳይነት በግሌ አጤንኩት፡፡ መንግስታቸዉና ገደብ ያጣ አመራራቸዉ በሕዝብ የተተፋ መሆኑን በሚገባ ስለሚረዱት ምርጫ በመጣ ቁጥር የመንፈስ ሠላም አጥተዉ ሕዝብንም ሠላም እንደሚነሱት ይታወቃል፡፡ በኃይል ስልጣን ላይ ለመቆየት በየወቅቱ የሚወስዷቸዉ ግብታዊ እና አምባገነናዊ እርምጃዎች የስንቶችን ሠላማዊ ዜጎች ኑሮና ሕይወት እንደቀጠፈ ለሁላችንም ግልፅ ነዉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚታይባቸዉ አምባገነናዊ ባህሪይ ግን ወደ ዉድቀት የማምራታቸዉን የመጨረሻዉ የተስፋ የመቁረጥ ጉዞ ብቻ ሳይሆን የአዕምሮ ጤንነታቸዉን ደረጃ እንድንጠራጠር ይገፋፋናል፡፡

***"የአሜሪካንን ድምፅ የአማርኛዉ ቋንቋ የሬድዮ ጣቢያ ስርጭት ጃም እንዲደረግ እደርጋለሁ፣ ከወዲሁ ማስረጃ አሰባስበን በተቃዋሚ ፓርቲ አንዳንድ ግለሰቦች ላይ ምርጫዉ በተጠናቀቀ ማግስት እንደሁኔታዉ ክስ እንመሰርታለን፣ ብርቱካን ሚደቅሳ ከእስር ቤት አትወጣም፣ አራት ነጥብ"*** በማለት የተናገሯቸዉ ንግግሮች ትምክህት ወይንም ማንአለብኝነት የነገሰበት አምባገነናዊ ባህሪያቸዉ ከመቼዉም ጊዜ በላይ እጅግ ጎልቶ እንዲወጣ ያደረገና ድንቅ ማንነታቸዉን ለወዳጆቻቸዉ ጭምር ያስመሰከረ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

በከፍተኛ ሙያዊ ስነ ምግባር የሚመራዉን እና ዘወትር ከሕዝብ የሚቀርብባቸዉን ትችት እና ድክመቶቻቸዉን ለማስተባበል የእራሳቸዉ መንግስት ባለስልጣናትን ሳይቀር ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚያስተናግደዉን የአሜሪካንን ድምፅ ሬድዮ ጣቢያ ከሩዋንዳዉ ሚል ኮሊንስ ጋር ለማመሳሰል መሞከራቸዉ አስገራሚ ነዉ፡፡

″የሞኝ ልቅሶ፣ መልሶ መላልሶ″ እንዲሉ  በሕዝብ ድምፅ ተሸንፈዉ ስልጣን ላለመልቀቅ «በትግራይና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ያለዉ ግንኙነት እንዲሻክርና የዘር ጥላቻ እንዲፈጠር ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ፀረ ሕዝብ ቅስቀሳ ያደርጋሉ፡፡ እኛ ከሥልጣን ከተወገድን ኢትዮጵያ የምትባል አገር አትኖርም፣ በሩዋንዳ የታየዉ ዓይነት የዘር ዕልቂት ይደርሳል» በማለት በየጊዜዉ የሚያሰሙት ማስፈራራት ዘንድሮ በተቃዋሚ ኃይሎች ምትክ በአሜሪካዉ ድምፅ የአማርኛ ቋንቋ ሬድዮ ጣቢያ ላይ ለምን እንዳነጣጠረ መገመት ቀላል ነዉ፡፡

በምርጫ 97 ወቅት የገጠማቸዉ ዓይነት የፖለቲካ ክስረትና ቅሌት ዳግመኛ እንዳይገጥማቸዉ በሁሉም መስክ የአምባገነን ኃይላቸዉ የሚፈቅደዉን ሁሉ አድርገዋል፣ በተለይም ነፃና ገለልተኛ ጋዜጠኞች እንዳይኖሩ፡፡ ከማያፈናፍን የሚዲያ ህግ ጋር ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ የሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ፀረ ሽብርን ለመቆጣጠር በሚል ሽፋን በጠቀላላዉ የምርጫዉን ሂደት ለማፈን፣ ዜጎች ሃሳባቸዉን በነፃነት የሚገልፁበት ምንም ዓይነት ቀዳዳ እንዳይኖር ለማድረግ ብዙ ደክመዋል፡፡  መለስና ካድሬዎቻቸዉ ምንም ያህል ቢደክሙ እንደ አሜሪካዉ ድምፅ የአማርኛ ቋንቋ አገልግሎት የሬድዮ ጣቢያዎች እያሉ እዉነቱ ሕዝብ ጆሮ መድረሱ እንደማይቀር ይገባቸዋል፡፡  ስለሆነም የድኃዉን ሕዝብ ማህበራዊ ሕይወት ለመደጎም መዋል ያለበትን የአገር ንዋይ ስርጭቱን ጃም ለማድረግ እንደሚጠቀሙበት ያለሀፍረት ለዉጭ አገር ጋዜጠኞች ገለፁ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ መስማት ያለበት እሳቸዉና ፓርቲያቸዉ የሚፈልገዉን ብቻ መሆን እንዳለበት በመናገር ለአገሪቱ ዜጎችና ለዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ያላቸዉን ንቀት አሳዩ፡፡

«መለስ ዜናዊና መንግስታቸዉ ተቃዋሚዎቻቸዉን ለማጥፋት በየጊዜዉ የሚያደርጉትን ጥረት ያህል የአገሪቱን ልማት ለማፋጠን ጥረት ቢያደርጉ ድህነትን ከኢትዮጵያ ምድር በየደረጃዉ ማስወገድ በተቻለ ነበር» በማለት አንድ የእንግሊዝ የፓርላማ አባል **የሁሉም ፓርቲዎች የፓርላማ ቡድን የ3ኛዉ ዓለም ትብብር/ All Party Parliamentary Group on the Third World Solidarity/** በመባል የሚጠራዉ ድርጅት በታላቋ ብሪታኒያ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት ጋር በመተባበር አምና በ2009 ባዘጋጀዉ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የሰጡት አስተያየት ምን ያህል ትክክለኛ እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነዉ፡፡

ከምርጫ 97 በኋላ አምባገነኑ የመለስ መንግስት ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን ለመተግበር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ይልቅ አብዛኛዉን ትኩረት የሰጠዉ መጪዉን ምርጫ ለማሸነፍ የሚረዱት የአፈና ስራዎችን በመስራት ነበር፡፡

ብሔራዊ የምርጫ ቦርዱ ነፃና ገለልተኛ እንዲሆን በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም በመንግስት በኩል የተወሰደዉ እርምጃ አስገራሚ ነዉ፡፡ የቦርዱ ሰብሳቢ በምርጫ 97 ኢህአዴግን ወክለዉ አዳማ ላይ ለተወካዮች ምክር ቤት ተወዳድረዉ በቅንጅት የተሸነፉ ሲሆኑ፣ ም/ዋና ፀኃፊና የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሆነዉ የተመደቡት ግለሰብ ወያኔ/ኢህአዴግ ያደራጀዉ የተለጣፊዉ የመምህራን ማህበር ዋና ፀኃፊ ሆነዉ አንጋፋዉን የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ያፈረሱ ቅጥረኛ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ ዓይነት የተደራጀዉ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ያለተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እዉቅና የተወዳዳሪነት የምስክር ወረቀት በመስጠት፣ አንዳንድ ህጋዊ የሆኑትን እንዳይመዘገቡ በመከልከል የሚፈፅመዉ ምስቅልቅል ቀላል አይደለም፡፡  እስከ ድምፅ መስጫ ጣቢያ ድረስ የምርጫ አስፈፃሚ ሆነዉ የተመደቡት ሰዎች ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል በየደረጃዉ በሚገኙ የመስተዳድር አባላት የተመለመሉ ናቸዉ፡፡ የምርጫዉ ካርድ በስራ ዕድል፣ በደመወዝ፣ በአበል፣ በእርዳታ እህል ስርጭት እና በሌሎችም ጥቅማ ጥቅሞች ወያኔ/ኢህአዴግ ሊያሸንፍ በሚችልበት መንገድ እየተገዛ ነዉ፡፡

በምርጫ 97 የፈፀሙትን ማጭበርበር ለዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ያጋለጠዉ እና በአዉሮፓ ህብረት የፓርላማ አባል በተከበሩ ወይዘሮ አና ጎሜዝ የተመራዉ ዓይነት ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢ ቡድን እንዳይመጣባቸዉ የወጣቶች እንዲሁም የሴቶች ፎረም አባላትን በተለያየ መንገድ በማደራጀትና በመደለል የራሳቸዉን አስመራጭና ታዛቢ ቡድኖችን ፈጥረዋል፡፡

ዛሬም ቅዠት ሆኖ የሚያስበረግጋቸዉን ቅንጅትን ዓይነት ጠንካራ ተቃዋሚ ኃይል እንዳይኖር ለማድረግ የተቃዋሚዉን ጎራ ለመከፋፈልና ለመበታተን ጥረት አድርገዋል፣ ብቻቸዉን ሩጠዉ ማሸነፋቸዉ እንዳያነጋግር ደካማ ተቃዋሚዎችን በተለያየ ዘዴ ከጎናቸዉ በማሰለፍ በከንቱ የስነ ምግባር መመሪያ እግር ተወርች አስረዋቸዋል፡፡

መንግስታዊ ያልሆኑ የረድኤት ድርጅቶች ጠ/ሚኒስትሩና ገዢ ፓርቲያቸዉ በማንአለብኝነት በሚፈፅሙት የሰብዓዊ መብት ረገጣ ዙሪያ ጣልቃ እንዳይገቡባቸዉ፣ የህግ የበላይነትን እና የዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ከማስፋፋት ተግባራት እንዲታቀቡ፣ አገር በቀል የሆኑትም መልካም

አስተዳደርን ለመፍጠር በሚደረገዉ እንቅስቃሴ፣ በፆታ እኩልነት፣ በህፃናትና በአካል ጉዳተኞች መብቶች እንዲሁም በግጭት ማስወገድ ተግባራት ላይ አንዳችም ተሳትፎ እንዳይኖራቸዉ በህግ አግደዋቸዋል።

የወያኔ/ኢህአዴግ ፓርቲን ዘረኛና አምባገነናዊ ፖሊሲ በማንኛዉም መልኩ የሚቃወሙ ዜጎችንና ድርጅቶችን ያለገደብ ለመወንጀል፣ ቢያንስ እስከ አራት ወር በፍ/ቤት ክስ ሳይመሰረት ለማሰር የሚያስችላቸዉን፣ በቀረበ ማስረጃ እስከ ሃያ ዓመት ሊያሳስር የሚችል፣ ፖሊስና የመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ያለፍርድ ቤት ማዘዣ በጥርጣሬ ብቻ በፈለጉት ሰዓትና ስፍራ ፍተሻ ሊያካሄዱ፣ ማስረጃ ነዉ የሚሉትን መዉሰድ እንዲያስችላቸዉ የሚረዳ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ አፅድቀዋል።

በአገሪቱ የሚገኙት የመገናኛ ብዙኃን ሙሉ በሙሉ በመንግስት ቁጥጥር ያሉ ሲሆን ገዢዉ ፓርቲ ትምክህትና ማንአለብኝነት በተመላበት መንገድ ለርካሽ የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳዉ የሚጠቀምባቸዉ ልሳን ናቸዉ። ነፃና ገለልተኛ የመገናኛ ተቋማት እንዳይስፋፉ፣ ዜጎች ሃሳባቸዉን በነፃነት የሚገልፁበት መንገድ እንዳይኖር ወያኔ ኢህአዴግ የተቻለዉን ሁሉ አድርጓል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፀደቀዉ አዋጅ ቀድሞ ከነበረዉ የፕሬስ ህግ እጅግ የከፋ ነዉ። ስልጣን ያላቸዉ የመንግስት አካላት መረጃ የመከልከል መብት እንዲኖራቸዉ፣ የፍትህ አካላቱ በሕዝብ ሰላምና በብሄራዊ ደህንነት ስም እንዳሻቸዉ ክስ እንዲመሰርቱ የሚፈቅድ፣ የማስታወቂያ ሚኒስቴር በፈቃድ መስጠትና ምዝገባ ስም ነፃ ሚዲያዎችን እንዲቆጣጠር የሚያደርግ፣ በየጥቃቅኑ ምክንያት በእስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ከመሆን አልፎ ተርፎ እስከ አንድ መቶ ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት በሙያዉ የተሰማሩ ጋዜጠኞችን ለማሰቃየት የፀደቀ ህግ ነዉ። ወያኔ/ ኢህአዴግ ያረቀቀዉን፣ ያፀደቀዉንና እመራበታለሁ የሚለዉን የራሱን ሕገመንግስት የሚፃረር፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት የሌለዉ የሚዲያ ህግ ነዉ።

እነዚህ በተከታታይ የወጡት ህጎች በምርጫ 97 ወቅት የገጠማቸዉ ዓይነት የፖለቲካ ክስረትና ቅሌት ዳግመኛ በዚህ በቀጣዩ ምርጫ እንዳይከሰቱ ለማድረግና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማፈን የታሰበባቸዉ ናቸዉ።

″ጌታዋን የተማመነች ዉሻ″ እንዲሉ መለስ ዜናዊ በአምባገነንነት የወሰዷቸዉ እነዚህ የመብት አፈናዎች የተፈፀሙት በአጥፍቶ ጠፊዎች ላይ በአፍሪቃ ቀንድ በሚደረገዉ ጦርነት ከምዕራቡ ዓለም በተለይም ከአሜሪካና ከብሪታኒያ መንግስታት ጋር በፈጠሩት ትብብር ምክንያት የሰላ ነቀፋና ማስፈራሪያ እንደማይገጥማቸዉ ባደረባቸዉ እምነት እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም። ያደረባቸዉ ከንቱ ትምክህት መጠኑን በማለፉ አወዳደቃቸዉን ወደ ሚያፋጥን ደረጃ ተሸጋገረ፣ ካለፉት ስህተቶቻቸዉ ከመማር ይልቅ ወደ ባሰ የጥፋት አዘቅት ዉስጥ ወደቁ። እሳቸዉ ብቻ ሳይሆኑ ከላይ እስከታች ያሉት የመንግስት ባለስጣኖቻቸዉ፣ የፓርቲ አባሎቻቸዉ፣ ካድሬዎቻቸዉና አፈቀላጤዎቻቸዉ እስከዛሬ እንደለመደባቸዉ በማስረጃ የተደገፈን እዉነት በሕዝብ አደባባይና በሚዲያ ቀርበዉ ለሰሚ በሚቀፍ መልኩ ከሚዋሹበት ድብቅ ሕይወት ተላቀዉ ማንነታቸዉን ይፋ አወጡት። ይህንን ያፈጠጠና ያገጠጠ ″የምን ታደርጉኛላችሁ?″ አቋም ትምክህት በተመላበት መልክ እንዲወስዱ የገፋፏቸዉ ሌሎች ምክንያቶችም እንዳሉ ግልፅ ነዉ።

- እኤአ በ1984 በተከሰተዉ የረሃብ አደጋ ከዓለም አቀፉ ህብረተሰብ በእነ ቦብ ጊልዶፍ ባንድ ኤይድ የተሰበሰበዉን የርዳታ እህል ድርጅታቸዉ በመሸጥ ሕዝብ በረሃብ ሲረግፍ ገንዘቡን ለጦር መሳሪያ መግዣ እንዳዋሉት በማያወላዳ ማስረጃ የተጠናቀረዉ የቢቢሲ ዘገባ የዓለም አቀፉ ህብረተሰብ የመነጋገሪያ አጀንዳ በመሆን የፓርቲያቸዉንና የአመራሩን አረመኔያዊ ድርጊት ያጋለጠ መሆኑ አንድ ምክንያት ነዉ። ከዚህ ባሻገር ወያኔ ነፃ አወጣዋለሁ ብሎ የሚነግድበትን የትግራይ ሕዝብ ለሰራዊት ምልመላ እንዲረዳዉ በነደፈዉና ባቀናበረዉ አረመኔያዊ ሴራ የፊልም መቅረጫ መሳሪያዎችን በተለያየ ስፍራ ተክሎ በመቅረፅ እኤአ በሰኔ 1988 በሃዉዜን ገበያ ሜዳ ላይ በደርግ ተዋጊ ጄት አዉሮፕላኖች ያስጨፈጨፈዉ ከ2500 የማያንስ የንፁኃን ዜጎች ጉዳይ ለጦር መሳሪያ መግዣ መዋሉን እንደሰማነዉ ርዳታ ወደፊት ልንሰማዉ እንችል ይሆናል።
- እኤአ በ2003 በጋምቤላ በአኝዋክ ብሄረሰብ አባላትና በቅርቡም በኦጋዴን አካባቢ ንፁኃን ዜጎች ላይ በተፈፀመዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ምክንያት በጠ/ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ላይ በዓለም አቀፉ የጦር ወንጀለኞች ፍርድ ቤት ክስ እንዲመሰረት የሚደረገዉ ግፊት እይተጠናከረ መሄዱ፣
- በአሜሪካ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት የዉጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የ2009 ሪፖርት በኢትዮጵያ ዉስጥ በዜጎች ላይ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ረገጣ፣ እስራትና እንግልት እንደሚደርስ ማጋለጡና ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ሊቀ መንበር

ወይዘሪት ብርቱኳን ሚደቅሳ ያለአግባብ በእስር ቤት የሚሰቃዩ የህሊና እስረኛ መሆናቸዉ መረጋገጡ፣

- የመንግስታቱ ድርጅት የሰብዓዊ መብት ድርጅት/ ሂዩማን ራይት ዎች/፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ ዓለም አቀፍ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ድርጅቶችና ሌሎችም የሲቪክ ማህበራት በኢትዮጵያ ዉስጥ ከጊዜ ወደጊዜ እየሰፋ በመሄድ ላይ ያለዉን ሙስና፣ የመብትና የህግ ጥሰት ያለመታከት መዘገባቸዉ፣
- የተቃዋሚዉን ጎራ ለመከፋፈልና ለማዳከም ወያኔ/ኢህአዴግ የተቻለዉን ሁሉ ቢያደርግም የስምንት የፖለቲካ ድርጅቶች ጥምረት የፈጠረዉ መድረክ እንደ 97ቱ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ሁሉ በሕዝብ ዉስጥ እየሰረፀ መግባት መጀመሩ፣
- ″ማንም አይመጣብኝም″ በሚል ትምክህት ሙሉ በሙሉ ህወሃት የግል የምርጫ ብቸኛ ምሽጉ አድርጎ በሚቆጥረዉ የትግራይ ክልል ዉስጥ በቅርቡ የተቋቋመዉ አረና የፖለቲካ ፓርቲ በሕዝብ ዘንድ ያለዉ ተቀባይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ የመለስ ዜናዊ ካድሬዎች አቶ አረጋዊ ገብረ ዮሃንስ በተባሉት በተቃማዊዉ የአረና ፓርቲ የተወካዮች ምክር ቤት ዕጩ ተወዳዳሪ ላይ የፈፀሙት ግድያ ልጆቹን በትግል ሜዳ የገበረዉን የትግራይ ሕዝብ ክፉኛ ማስቆጣቱ፣

በጠቅላላዉ ሳይጀመር የተጠናቀቀዉን የ2002 ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ ለማስመሰልና ለማታለል ላለፉት 5 የስልጣን ዓመታት መለስና ካድሬዎቻቸዉ ደፋ ቀና ያሉበት የማጭበርበር ተግባር እንዳሰቡት ሊጠናቀቅ ያለመቻሉ አዕምሯቸዉን እንዳቆሰለዉ አይካድም:: በአስመሳይነትና በብልጣ ብልጥነት ″ገነባሁት″ ያሉት ማንነታቸዉ ከዓመት ዓመት እየተሸረሸረ መሄዱን በዉል ያጤኑት አይመስልም:: ማን አለብኝነት የነገሰበት ትምክህት ስብዕናቸዉን ስለተቆጣጠረዉ መነሻቸዉን ዘነጉት:: ከመንግስቱ ኃይለማርያም አምባገነን ስርዓት ለመገላገል ድጋፉን ከቸራቸዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባሻገር ለዚህ ስልጣንና ክብረት ያበቋቸዉ ምዕራባዊያን መንግስታትና በተለይም ልጆቹን የገበረዉ የትግራይ ሕዝብ እንደሆነ በፍፁም ሊታሰባቸዉ አልቻለም:: ከዚህ በኋላ ለሁሉም ነገር መልስ መስጠት የሚችሉ፣ ማንንም ለማሸነፍ ኃይልና ብቃት ያላቸዉ፣ የማንም እርዳታና ትብብር የማያስፈልጋቸዉ ትንሹ እግዚአብሄር አድርገዉ እራሳቸዉን በቆጠሩበት ደረጃ ላይ የደረሱ ይመስላል::

***"የአሜሪካንን ድምፅ የአማርኛዉ ቋንቋ የሬድዮ ጣቢያ ስርጭት ጃም እንዲደረግ እደርጋለሁ፣ ከወዲሁ ማስረጃ አሰባስበን በተቃዋሚ ፓርቲ አንዳንድ ግለሰቦች ላይ ምርጫዉ በተጠናቀቀ ማግስት እንደሁኔታዉ ክስ እንመሰርታለን፣ ብርቱካን ሚደቅሳ ከእስር ቤት አትወጣም፣ አራት ነጥብ"*** በማለት የሰጧቸዉ አምባገነናዊ መልሶች የዉድቀታቸዉ አመላካች ናቸዉ:: አምባገነኖች በመጨረሻዋ የጣዕረ ሞት ሰዓታቸዉ ከዚህ ዉጭ እንደማይሆኑ በታሪክ የታየ ሃቅ ነዉና መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸዉ ከማለት በስተቀር ምን ማለት ይቻላል? ሁሉንም ዕድሜ ሰጥቶን ለማየት ያብቃን!